የህፃናትን ደህንነት ለመንከባከብና ህፃናትን ከተለያዩ አደጋዎችና ጥቃቶች ለመጠበቅ የወላጆች ሚና

ማውጫ


አጠቃላይ መመሪያ.......................................................................................... 2

የስልጠናው አላማ............................................................................... 2

ክፍል አንድ፡ የህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ያለው ጠቀሜታ ............................................ 5

ህፃናትን የሚጎዱ ድርጊቶች...................................................................... 9

1. አካላዊ ጥቃት....................................................................... 9
2. የአእምሯዊ ስሜት ጥቃት..............................................................9
3. ወሲባዊ ጥቃት......................................................................... 11
4. ቸልተኝነት..............................................................................13

በልጆች ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ድርጊቶች የሚያስከትሉት ጉዳት ምንድን ነው?......................... 13

ቁልፍ መልእክቶች.......................................................................... 14

ክፍል ሁለት፡ ወላጆች / አሳዳጊዎች እንዴት የህፃናት ደህንነትን ማረጋገጥ ይችላሉ?................ 16

የውይይቱ ዓላማ............................................................................... 16

ቁልፍ መልእክቶች............................................................................ 21

ለአወያይ ተጨማሪ መረጃ....................................................................... 22

ህፃናት ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያመላክቱ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማወቅ.................. 23

ህፃናትን ከጥቃት ለመከላከል ምን ማድረግ ያስፈልጋል?.......................................... 26

በልጆች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል እንዲቻል ለወላጆች ተጨማሪ ጥቆማዎች......... 28

የጨቅላ ህፃናት ደህንነትና ጥበቃ......................................................... 31

ልጆች ላይ በድንገተኛ አደጋ ለሚደርስ ጉዳት ወላጆች ማድረግ ያለባቸው ዝግጅትና እርምጃ.......32


የህፃናትን ደህንነት ለመንከባከብና ህፃናትን ከተለያዩ አደጋዎችና ጥቃቶች ለመጠበቅ የወላጆች ሚና

የስልጠናው አላማ ፡ በስልጠናው መጨረሻ ወላጆች/አሳዳጊዎች

- የሕፃናትን ደህንነት በአግባቡ ለመንከባከብና ህፃናትን ከተለያዩ አደጋዎችና ጥቃቶች ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግና ምን ማድረግ እንደሚቻል ግንዛቤ ይጨብጣሉ።

የስልጠናው ተሳታፊዎች

የስልጠናው ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የሚጠበቁት መምህራን፣ ህፃናትን በሚንከባከቡ ድርጅቶች የሚሰሩ ሰራተኞች እንዲሁም ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ናቸው።

ክለሳ

በየስልጠናው መጀመሪያ እያንዳንዱ ሰልጣኝ ባለፈው የተማረውን ለማስታወስ እንዲረዳው በሁለት ተሳታፊዎች ያለፈው ውይይት ፍሬ ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፦

1. ባለፈው የተወያየንባቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
2. ባለፈው ከተወያየንበት ርእሰ ጉዳይ አንፃር በቤታችሁ ከልጆቻችሁ ጋር ምን አደረጋችሁ? ያጋጠማችሁ ችግር ነበር ወይ?
3. ያለፈውን ትምህርት ለጎረቤቶቻችሁ አካፈላችሁ?

ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ምዘና

እያንዳንዱ የስልጠና ክፍል ከመጀመሩ በፊት ለተሳታፊዎች የቅድመ-ስልጠና ምዘና ይሰጣቸዋል። በስልጠናው የቀሰሙትን እውቀት ለመገምገም ደግሞ የድህረ-ስልጠና ምዘና በእያንዳንዱ የስልጠና መጨረሻ ላይ ይሰጣል።

አጠቃላይ የስልጠና ደንቦች፤

> አወያይ
>
> በስልጠናው የመጀመሪያ ቀን የሚከተሉትን የስልጠናውን ደንቦች ለተሳታፊዎቹ ያሳውቋቸው

- የሰልጣኞች አቀማመጥ በግማሽ-ክብ ቢሆን እንደሚመረጥ ማሳወቅ
- የአወያይ እና የተሳታፊዎች ትውውቅ ማካሄድ
- በሰአት መገኘት
- በስልጠናው ወቅት የሞባይል ስልክ ጥሪን በንዝረት /Vibration/ ላይ ማስቀመጥ
- በእያንዳንዱ የስልጠና ክፍለ-ጊዜ መገኘት
- ንቁ ተሳትፎ ማድረግ
- የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ ማክበር
- የክለሳ ክፍለ ጊዜ - በየእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ባለፈው ቀን የተማሩትን ትምህርት በተመለከተ በአጭሩ ገለፃ የሚያደርጉ ሁለት ተሳታፊዎችን በመሰየም ለአምስት ደቂቃ ማወያየት
- የስልጠና ቦታውን ማስተካከል - በየእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ለአስር ደቂቃ ያህል የስልጠናው አስተባባሪዎች የስልጠናውን ቦታ እንዲያመቻቹ ማድረግ
- ሰአት ተቆጣጣሪ መምረጥ

የሚያስፈልጉ ቁሶች

- በህፃናት እድሜ ደረጃ የተዘጋጁ የተረት ወይም የታሪክ መፅሃፍት እና ስእሎች
- ንፁህ የመፃፊያ ሰሌዳ / ፍሊፕ ቻርት
- ማርከር
- ብዕር እና የማስታወሻ ደብተር
- በራሪ ፅሁፎች

በእያንዳንዱ ስልጠና የሚያዝ ማስታወሻ

በእያንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ ላይ አወያይ ስለ ውይይቱ ሂደት ማስታወሻ እንዲይዙ ይጠበቃል። ለውይይቱ በሚያደርጉት ዝግጅት ወይንም በውይይት ሂደት ውስጥ ነጥረው የወጡና በምእራፉ ውስጥ ሊካተቱ ወይም በድጋሚ ሊጤኑ የሚገቡ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል። እነዚህ ፍሬ ሀሳቦች በአሰልጣኞች ስልጠና ወቅት ውይይት እየተደረገባቸው ይህንን ሰነድ ወደፊት የበለጠ ለማዳበር ይረዳሉ።

**ተግባር 1፡ ያለፈውን የውይይት መርሀ ግብር መከለስ (አምስት ደቂቃ)**

| |
|---|
| አወያይ<br><br>ሁለት ፈቃደኛ ተሳታፊዎች ያለፈውን የውይይት ፍሬ ሀሳቦችን እንዲያስታውሱ በሚከተለው ሁኔታ ይጠይቁ |

1. ባለፈው የተወያየንባቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?

2. በስልጠናው የቀሰማችሁትን ለሌሎች ሰዎች አካፈላችሁ?

ክፍል አንድ፡ የህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ያለው ጠቀሜታ

ተግባር ሁለት፡ የቡድን ውይይት

> አወያይ
>
> ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን ለውይይት እንዲያዘጋጁ ለማገዝ የህፃናት ደህንነት እና ጥበቃ ለምን እንደሚያስፈልግ ከዚህ በታች የተቀመጡ ነጥቦችን ለተሳታፊዎች ይግለፁላቸው።

ብዙዎች ህፃናት በቤት ውስጥ ወይንም ከቤተሰብ ጋር ከሆኑ ደህንነታቸው እንደተጠበቀ ያስባሉ። ነገር ግን አንዳንድ ቤተሰብ በቤት ውስጥና በአካባቢያቸው ለህፃናት ደህንነት የሚያሰጉ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን በእቅድ ክትትል አያደርጉም። የሚያሰጉ ሁኔታዎች ካሉ ወይንም ወላጆች የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ በቂ ትኩረት ካልሰጡ የልጆች ደህንነት አደጋ ውስጥ ይወድቃል። ደህንነቱ ያልተጠበቀ አካባቢ የሚባለው በህፃናት ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ስፍራ ነው።

- የህፃናት ደህንነት ጥበቃ በህፃናት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚወሰድ የመከላከል እርምጃ ወይንም በህፃናት ላይ እየደረሰ ያለ ጉዳትን የማስቆም ተግባር ነው።

- ህፃናት ራሳቸውን የመከላከል አቅም ስለሌላቸው ደህንነታቸውን ማስጠበቅ የወላጆችና የሚኖሩበት ማህበረሰብ ሀላፊነት ነው።

- ወላጆች ልጆቻቸውን በህፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንዲሁም እንዴት ከአደጋ ማምለጥ እንደሚችሉ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል።

- ወላጆች በልጆቻቸው ላይ የህፃናትን ደህንነት፣ ክብርና እድገት የሚጎዱ የተለያዩ መጥፎ ተግባራት እንዳይደርስ ተገቢ ጥንቃቄና ክትትል ማድረግ አለባቸው።

- ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የተለያየ አደጋ እንዳያጋጥማቸው አስቀድሞ መጠንቀቅ ተገቢ ነው።
- በህፃናት ላይ በተለያዩ ሰዎች አካላዊ፣ ስሜታዊ እንዲሁም ፆታዊ ጥቃት ይፈፀማል።
- አንዳንድ ወላጆች ህፃናትን ስርአት ለማስተማር በማሰብ በልምጭና በቀበቶ ይገርፋሉ፣በጥፊ ይማታሉ፣አናታቸውን በኩርኩም ይማታሉ፣ ይራግጣሉ፣ ይቆነጥጣሉ፣ በስድብና በጩኸት ይቆጣሉ፣በስደብና በማስፈራራት ያሸማቅቃሉ፣በገመድ በማሰር፣በጋለ ብረት በማቃጠል እንዲሁም በርበሬ በማጠን ይቀጣሉ።
- ሌሎች ሰዎች ደግሞ በህፃናት አእምሮ፣ እድገት፣ ጉልበትና ህይወት ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ጎጂ ተግባራት ይፈፅማሉ።

የውይይቱ አላማ

በውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎች ፡

- የህፃናት ደህንነትና ጥበቃን አስፈላጊነት በመገንዘብ በልጆች ላይ አደጋ የሚያደርሱ ተግባራት የሚቀንሱበት ስልቶችን ይናገራሉ።
- ለህፃናት ደህንነት አስጊ የሆኑ ተግባራትን ይለያሉ።
- በህፃናት ደህንነት ላይ አደጋ የሚያደርሱ ሁኔታዎችን በመለየት የመፍትሄ እርምጃዎችን ይገልፃሉ።

አወያይ

የውይቱን አላማዎች ለሥልጠናው ተሳታፊዎች ያንብቡላቸው

አወያይ

1. ተሳታፊዎች በሶስት ቡድን እንዲደራጁ ያድርጉ

2. እያንዳንዱ ቡድን የራሱን አወያይ ይመርጣል። እንዲሁም የውይይቱን ቃለ ጉባኤ የሚፅፍና በኋላ ለተሰብሳቢው የሚያቀርብ አንድ ሰው ከየቡድኑ መመረጥ ይኖርበታል።

3.ለእያንዳንዱ ቡድን የተለያዩ አጫጭር ትረካዎችን የሚገልፁ ፅሁፎችን በመስጠት ታሪኩን አንብበውና በታሪኩ ላይ ተወያይተው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ

የውይይቱ ተሳታፊዎች ቀጥሎ የሚቀርቡትን አራት ገጠመኞች ካነበቡ በኋላ የእያንዳንዱ ቡድን አባላት የሚከተለውን ጥያቄ እንዲመልሱ ይንገሯቸው።

ለውይይቱ ተሳታፊዎች የሚቀርቡ ሁለት ጥያቄዎች፡

1. ከሰማችሁት ታሪክ ውስጥ በህፃናት ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉት ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?
2. በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱ ህፃናት መጨረሻቸው ምን ሊሆን ይችላል?

## ታሪክ አንድ - ደበላ

ደበላ ከበደ መልከ መልካም የአራት ዓመት ህፃን ልጅ ነው። ወላጆቹ ዘወትር ይጣላሉ። ደበላ ከሁለት አመቱ ጀምሮ አባቱ ዘወትር እናቱን በጩኸት እየተሳደቡ ሲደበድቡ ይመለከታል። እናቱ ሲደበደቡ ይጮሃሉ። ደበላም የእናቱን ጩኸት ተከትሎ አብሮ ይጮሃል። በዚህ የተነሳ አባቱን መፍራት ጀምሯል። እንዲያውም አባቱ ሲይዙት መጮህ ጀምሯል። በቅርቡ ደግሞ በአካባቢው ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲናገሩ ከሰማ በፍርሃት ያለቅሳል። ከእናቱ ጋር ወደ ገበያ ሲሄድ ሌሎች ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲናገሩ ከሰማ ጮሆ ያለቅሳል። እናቱ የሚያለቅሰውን ልጅ ለማባበል በጣም ትቸገራለች።

## ታሪክ ሁለት - እርጎዬ

ወይዘሮ እርጎዬ የሶስት ልጆች እናት ናት። ባለቤቷ በመሞቱ ልጆቹን የምታሳድጋቸው የቀን ስራ እየሰራች ነው። ወደ ስራ ስትሄድ የመጨረሻ ልጇን ይዛ ትሄዳለች። ወደ ስራ ስትሄድ ቤቷ እንዳይዘረፍ ስለምትፈራ በሩን ዘግታ ሁለቱ ልጆቿ ጎረቤት ቤት ሄደው እንዲጫወቱ ታደርጋለች። ጎረቤቶቿ ልጆቿን እንዲያዩላት ትናገራለች።

የወይዘሮ እርጎዬ ልጆች እናታቸው እስክትመጣ ቤታቸው ፊት ለፊት እየተጫወቱ ይቆያሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከመንገድ ላይ ወድቆ የሚያገኙትን ጓንት፣ ባዶ የውሃ መያዣ ፕላስቲክ፣ ወረቀት እንዲሁም የህክምና መርፌ እየሰበሰቡ በማምጣት ይጫወታሉ። በላስቲክ ከረጢት ውስጥ የሚገኙ ምግቦችን እያነሱ ይመገባሉ። በመንገድ ላይ ትላልቅ ልጆች ሲሳደቡ የሰሙትን መጥፎ ቃላት እነርሱም ሲጣሉ ይጠቀሙበታል።

## ታሪክ ሶስት- ጀሚላ

ጀሚላና መንታ ወንድሟ ከድር የሰባት አመት ልጆች ናቸው። ከድር ሁልጊዜ ከሰፈር ልጆች ጋር ሲጫወት ጀሚላ ግን በቤት ውስጥ እናቷን በስራ እንድታግዝ እንጂ ከቤት እንድትወጣ አይፈቀድላትም። ነገር ግን በቤት ውስጥ ስራ ከሌለ እናቷ ጀሚላ ከከድር ጋር ወደ ውጪ ወጥታ ከሰፈር ልጆች ጋር እንድትጫወት ትፈቅድላታለች። ከተማው በግርግር የተሞላ በመሆኑ ለልጆች መጫወቻ ሜዳ የለም። ስለዚህም ልጆች ከትምህርት ቤት ከመጡ በኋላ መክስሳቸውን በልተው በመንገድ ላይ ሽቅብና ቁልቁል ሲሮጡ እንዲሁም በየትበው ሲጫወቱ ያመሻሉ። በመንገዱ ላይ በየአቅጣጫው ብዙ ሰዎች፣ ውሾች፣ አህዮች፣ የቀንድ ከብቶችና ተሽከርካሪዎች ይተላለፋሉ። ልጆች ደግሞ ዘወትር አጥር ላይና በመንገድ ዳር በተተከሉ ዛፎች ላይ ሲንጠላጠሉና ሲደባደቡ ያመሻሉ። ከድርና ጓደኞቹ ሲደባደቡ የሚመለከቱ አንዳንድ መንገደኞች እንዳይጣሉ ይመክሯቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ እየሳቁ ይበልጥ እንዲደባደቡ ያበረታቷቸዋል። ጥቂት ሰዎች ደግሞ በጣም በመግረፍ ይቀጧቸዋል።

## ታሪክ አራት- የሚሚና የአስጠኚዋ ታሪክ

ሚሚ የሰባት አመት ልጅ ስትሆን የአንደኛ ክፍል ተማሪ ናት። ሚሚ የምትኖረው ከወላጆቿና ከሁለት ታላላቅ ወንድሞቿ ጋር ነው። የሚሚ አባት ካህን ሲሆኑ እናቷ ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን ነገር በሀላፊነት ያስተዳድራሉ። ጎረቤታቸው የሚገኘው አቡ የተባለው የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሚሚን በሳምንት ለሶስት ቀናት ያስጠናታል። አቡ የአስራ አምስት ዓመት ልጅ ነው። ሚሚ ትምህርቷን እንድታጠና እንዲሁም የቤት ስራ እንድትሰራ አቡ ያግዛታል። አቡ ጨዋ በመሆኑና ሚሚን በመርዳቱ የተነሳ የሚሚ ወላጆችና ሚሚ አቡን

ይወዱታል። አቡ ሚሚን የሚያስጠናት በሚሚ መኝታ ቤት አልጋ ላይ ተቀምጠው ነው። አቡ ሚሚን የቤት ስራ ሲያሰራት በጣም ተጠግቶ በመቀመጥ እንዲሁም ስትፅፍ ለማገዝ በትከሻዋ በኩል እጁን አጥብቆ ይይዛታል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የለበሰችውን ሱሪ ይይዛል። በተጨማሪም ከንፈሯንና ጡቶቿን ይዳብሳል። አቡ እንዲህ ሲነካካት ሚሚ ደስ ይላታል።

ለውይይቱ ተሳታፊዎች የሚቀርቡ 2 ጥያቄዎች፡

1. ከሰማችሁት ታሪክ ውስጥ በህፃናት ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉት ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?

2. በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱ ህፃናት መጨረሻቸው ምን ሊሆን ይችላል?

የቡድኖችን ሪፖርት ማድመጥ (ሀያ ደቂቃ)

አወያይ፡

1. ተሳታፊዎች ከላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ከተወያዩ በኋላ በተወካዮቻቸው አማካኝነት በየተራ መልሶቻቸውን ለተሳታፊዎች መግለፅ ይኖርባቸዋል።

2. ለእያንዳንዱ ቡድን አቅራቢዎች አምስት አምስት ደቂቃ ብቻ በመፍቀድ የቡድናቸውን መልስ እንዲያቀርቡ

3. አንዱ አቅራቢ ሲጨርስ ሁለት ተሳታፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ ወይንም ጥያቄ እንዲያቀርቡ ይፈቀድላቸው።

ከተሳታፊዎች በተሰጡ አስተያየቶች ላይ አወያይ እርማት መስጠት ወይም ሀሳቡን ማጠናከር ይኖርባቸዋል።

ፍተሻ (ክለሳ)፡ (አምስት ደቂቃ)

አወያይ

ሁለት ተሳታፊዎችን ይምረጡና ስለ ህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ምንነትና ጠቀሜታዎች በአጭሩ እንዲያብራሩ ይጠይቋቸው። ለፍተሻ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹ በእለቱ ምን ያህል እንደተማሩ ለመገምገም የሚቀርቡ እንጂ ፈተና ያለመሆኑ ለወላጆች ሊገለፅላቸው ይገባል።

## ህፃናትን የሚጎዱ ድርጊቶች

አወያይ

የህፃናትን ደህንነት፣ ጤና፣ ክብርና እድገት የሚጎዳ መጥፎ የአያያዝ ሁኔታ ህፃናትን ማጎሳቆል ይባላል። በህፃናት ላይ የሚፈጸሙ የተለያዩ የማጎስቆል ድርጊቶች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ሆን ተብለው በአላማ የሚፈፀሙ ህፃናትን የማጎስቆል ድርጊቶች የመኖራቸውን ያህል አዋቂዎች እና ወጣቶች ባለማወቅ በህፃናት ላይ የጥቃት ድርጊት ያደርሳሉ። ህፃናትን ማጥቃት ድርጊት ህግን መጣስ ነው። በህፃናት ላይ የሚደርሱ የተለያዩ የጥቃት ድርጊቶች አሉ። እነኚህም፡ አካላዊ ጥቃት፣ የአእምሯዊ ስሜት ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃትና ችላ ማለት ናቸው።

በልጆች ላይ የሚደርሱ የጥቃት አይነቶች

1. አካላዊ ጥቃት፡ ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ልጆችን በመደብደብ ወይንም በማቁሰል ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ። አካላዊ ማጎስቆል ቁንጥጫን፣ ጥፊን፣ ድብደባን፣ መነቅነቅን፣ ማቃጠልን፣ ልጆችን መወርወርንና የመሳሰሉትን ያካትታል።

2. የአእምሯዊ ስሜት ጥቃት፡ በማወቅ ለመጉዳት ብሎ ወይም በለማወቅ ልጅን ስነስርአት

አወያይ

ልጆች ላይ አካላዊ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶች አካላዊ ጥቃት ይባላሉ። ድርጊቶቹ የሚፈጸሙት ሆን ብሎ ልጅን ለመጉዳት ወይም ልጅን ለመቅጣት በሚል ሰበብ ሊሆን ይችላል።

ባለማወቅ ድርጊቱን የሚፈፅሙ ሰዎች ምክንያታቸው ልጆችን መልካም ስነ ስርአት ለማስተማር የሚጠቅም ምቹ የጥፋት ማረሚያ ዘዴ እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን በአካላዊ ቅጣት/ማጎስቆል የሚደረገው ስነስርአት ማስያዝ ህፃንን ለህመምና ለሌሎች አካላዊ ጉዳቶች ከመዳረጉ በተጨማሪ በህፃን  ባህርይ ላይ ችግሮችን ያስከትላል። ልጆችን ስነ ስርአት የምናስተምረው ስህተት የሆነውን ተግባር ከትክክለኛው ለይቶ በማስተማርና ጥብቅ ክትትል በማድረግ እንጂ ልጆችን በህመምና በፍርሃት እንዲኖሩ በማድረግ አይደለም። አካላዊ ጥቃት ስነ ስርአት ከማስተማር ይልቅ ልጆችን ይጎዳል። ልጅን በአካላዊ ቅጣት ለማረም የሚደረጉ ድርጊቶች ለልጆች አጉል ልማድን ያስተምራሉ። ከቁንጥጫና ኩርኩም ጀምሮ ልጅን ስለት ባላቸው ነገሮች መቁረጥና መውጋት እንዲሁም በጋሉ ነገሮች ማቃጠል የመሳሰሉት ተግባራት ሁሉ በህፃናት ላይ የተለያዩ አካላዊና የባህርይ ችግሮችን ያስከትላሉ።

አወያይ

በህፃናት ላይ የአእምሯዊ ስሜት ጥቃት የሚያደርሱት ትላልቅ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የእድሜ እኩዮቻቸውም ጭምር ናቸው። ይህ ደግሞ በቤተሰብ ውስጥና በጨዋታ ጓደኞቻቸውም ሊፈፀም ይችላል። ዘወትር ልጆችን ማዋረድ፣ መግፋት፣ መውቀስ፣ ማስፈራራት፣ ማግለል እንዲሁም ከወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጋር የማይገባ ውድድር ማድረግ ልጆችን በስሜት ማጎሳቆል ነው። ልጆችን በስሜት ማጎሳቆል ለልጆች ፍቅርን፣ ስሜታዊ ድጋፍንና አመራር አለመስጠትን ያጠቃልላል።

በህፃናት ላይ ለረዥም ጊዜ የሚታይ የስነ ልቡና ችግር ከአእምሯዊ ስሜት ጥቃት ጋር ሊያያዝ ይችላል። ለምሳሌ ያለ በቂ ምክንያት ከልጆች ከፍተኛ የትምህርት ውጤት የምንጠብቅ ከሆነና ልጆች ያንን ውጤት ማምጣት ስላልቻሉ ብቃት እንደሌላቸው ደጋግመን ስንነግራቸው ስሜታቸው ይጎዳል። በዚህም ብቁ አለመሆናቸውን በማሰብ ለረዥም ጊዜ በሚታይ የስነ ልቡና ችግር ሊሰቃዩ ይችላሉ።

**3.** ወሲባዊ ጥቃት

አወያይ

ትላልቅ ሰዎች ወይንም በእድሜ ከፍ ያሉ ልጆች ከህፃናት ጋር ወሲባዊ ተግባር ከፈፀሙ ወሲባዊ ጥቃት ይባላል። በህፃን ላይ ወሲባዊ ጥቃት የሚፈፀመው ሰዎች ህፃንን በማባበልና በማታለል፣ በመደለል፣ በማስፈራራት ወይንም በማስገደድ ሊሆን ይችላል።

የህፃናት ወሲባዊ ጥቃት በተለያየ መንገድ ሊፈፀም ይችላል። ለምሳሌ፡

1. ከህፃናት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈፀም
2. ህፃናትን ልብስ አስወልቆ የመራቢያ አካላቸውን ማየት ወይም መነካካት

3. የራስን ልብስ አውልቆ ሰውነትን ለህፃናት ማሳየት
4. ህፃናት ወሲባዊ ተግባራትን ወይንም የመራቢያ አካላትን የሚያሳዩ ስእሎችን ወይንም ምስልና ድምፅ /ቪዲዮ/ እንዲመለከቱ መፍቀድ
5. ህፃናትን ለወሲባዊ ንግድ መጠቀም
6. የህፃናትን ልብስ አስወልቆ የመራቢያ አካላቸውን ምስል ማንሳት
7. ህፃናት የሌሎችን ሰዎች የመራቢያ አካል እንዲነካኩ ማበረታታት ወይንም ማስገደድ
8. ህፃናት በወሲባዊ ተግባር እንዲሳተፉ ማበረታታት ወይንም ማስገደድ
9. የወሲብ ስእሎችን ማሳየት፣ ፊልሞችን ማሳየት ቴም ህፃናት ወሲባዊ ውይይቶችን እንዲሰሙ ማድረግ

ከላይ የተዘረዘሩትና መሰል ድርጊቶች ሁሉ የህፃናት መብትን በመጣስ የሚፈፀም የጥቃት ወንጀል ነው።

አወያይ

ወንዶችና ሴቶች ልጆች በየትኛውም እድሜ ደረጃ ወሲባዊ ጥቃት ሊፈፀምባቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ ህፃናት በሚያውቁትና በሚያምኑት ሰው ወሲባዊ ጥቃት ሊፈፀምባቸው ይችላል። ወሲባዊ ጥቃት የተፈፀመባቸው ህፃናት በተለያየ ምክንያት የደረሰባቸውን ጥቃት አይናገሩም። ብዙ ጊዜ በባህል እንዲህ አይነት ጥቃቶች እንዲነገሩ ስለማይበረታቱ ህፃናት ለመናገር ያፍራሉ። ጥቃት የተፈፀመባቸው ህፃናት ጉዳዩን ለማንም ሰው እንዳይናገሩ በጥቃት ፈፃሚው ማስፈራሪያ ስለሚሰጣቸው ለወላጆቻቸውም ቢሆን የደረሰባቸውን አይናገሩም። በተጨማሪም ጥቃት የደረሰባቸው ህፃናት ለችግሩ ራሳቸውን ተጠያቂ በማድረግ፣ ራሳቸውን ጥፋተኛ አድርጎ በመቁጠርና ከወላጆች የሚገጥማቸውን ቁጣ በመፍራት ስለ ደረሰባቸው ጥቃት መናገር አይፈልጉም።

## **4.** ቸልተኝነት (አስፈላጊ ለሆኑ የህፃናት ፍላጎቶች ምላሽ መንፈግ ወይም ህፃናትን ከአደጋና ጥቃት አለመጠበቅ)

የህፃናትን መሰረታዊ ፍላጎት ማለትም ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ እንቅልፍ፣ ህክምና፣ ትምህርትና የመሳሰሉትን እንዳያገኙ ማድረግ፣ ፍቅር አለመስጠት እንዲሁም ከጥቃት አለመጠበቅ ለህፃናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ ወይንም ቸልተኝነት ነው። ይህም በማወቅ ወይም ባለማወቅ ሊፈፀም የሚችል የህፃናት

ጥቃት ነው። ለህፃናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ ወይንም ቸልተኝነት ማሳየት በህፃናቱ ላይ አእምሯዊ ጉዳቶችን ያስከትላል። በዚህ አይነት ያደጉ ልጆች ከሌሎች ይልቅ በትምህርትና በማህበራዊ ክዋኔያቸው ዘገምተኛ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው።

አወያይ

ቸልተኝነት ወላጆች ለልጆቻቸው ማድረግ ስለሚገባቸው ተገቢ እንክብካቤ ባለማወቃቸው ወይንም ባለባቸው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ሊፈጠር ይችላል።

## በልጆች ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ድርጊቶች የሚያስከትሉት ጉዳት ምንድን ነው?

አወያይ

ሁሉም አይነት ማጎሳቆሎችና ለህፃናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ በህፃናት ላይ ጠባሳ ያሳርፋሉ። ጠባሳዎቹ አካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም አካላዊና ስሜታዊ ሊሆኑ ይችላሉ። እንደማጎሳቆሉ ብዛትና ክብደት ጠባሳዎቹ እስከ ህይወት መጨረሻ ሊዘልቁ ይችላሉ። በተለይ በአእምሯዊ ስሜት ላይ የሚደርሱ ጠባሳዎች የህፃናትን የማንነት ስሜትን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን፣ በስራና በትምህርት ስኬትን በጣም ሊያበላሹ ይችላሉ።

**ቁልፍ መልእክቶች(አምስት ደቂቃ)**

አወያይ

ቁልፍ መልእክቶችን ያብራሩላቸው

- ህፃናት በሚውሉበት ስፍራ አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል።
- በአንዳንድ ትላልቅ ሰዎች በህፃናት ደህንነት፣ ጠባይና ህይወት ላይ የሚፈፀሙና አደጋ የሚያስከትሉ ድርጊቶችን መፈፀም ልጆችን ማጎሳቆል ይባላል። ህፃናትን አለመንከባከብ ወይንም ችላ ማለት የልጆች መጎሳቆልን ያስከትላል። በህፃናት ላይ የሚፈፀም ጎጂ ድርጊትና ቸልተኝነት በማደግ ላይ የሚገኙ ህፃናትን አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወሲባዊና አእምሮአዊ እድገትን ወደ ችግር ያስገባል።
- ቁንጥጫ፣ ጥፊ፣ ድብደባ፣ መወዝወዝ፣ ማቃጠል ወይንም መወርወር አካላዊ ማጎሳቆል ነው።

- ዘወትር ልጆችን ማዋረድ፣ መግፋት፣ መውቀስ፣ ማስፈራራት፣ ማግለል እንዲሁም ከወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጋር የማይገባ ውድድር ማድረግ ልጆችን በስሜት ማጎሳቆል ነው።
- ህፃናትን በማታለል ወይንም በማስገደድ የሚፈፀም የወሲብ ድርጊት ልጆችን በወሲብ ማጎሳቆል ነው። ልጆችን በወሲብ ማጎሳቆል በሚከተሉት ድርጊቶች ይገለፃል፡
    - ✓ ለህፃናት ስለ ወሲብ በማውራት
    - ✓ በወሲባዊ ስሜት የህፃናትን ሰውነት መነካካት
    - ✓ ለህፃናት የአዋቂዎችን የስነ ተዋልዶ አካላት ማሳየት፣ የወሲብ ስእሎችን በማሳየት
    - ✓ የወሲብ ድርጊትን የሚገልፁ ታሪኮችን በማውራት
    - ✓ ህፃናት እያዩ ወሲባዊ ድርጊት መፈፀም
- መሰረታዊ ፍላጎትን ማለትም ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ እንቅልፍ፣ ህክምና፣ ትምህርትና የመሳሰሉትን እንዳያገኙ ማድረግ እንዲሁም ከጥቃት ከለላ አለመስጠት ለህፃናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ ወይንም ቸልተኝነት ነው።

ሁሉም አይነት ማጎሳቆሎችና ለህፃናት ፍላጎት ምላሽ መንፈግ በህፃናት ላይ ዘላለማዊ ጠባሳ ያሳርፋሉ። አንዳንዶቹ ጠባሳዎች አካላዊ ሲሆኑ ስሜታዊ ጠባሳዎች ግን እስከ ህይወት መጨረሻ የሚዘልቁ አሉታዊ ተፅእኖዎች በማሳረፍ የህፃናትን የማንነት ስሜት ሳይቀር ያጠፋሉ።

ማጠቃለያና የቤት ስራ (አምስት ደቂቃ)

አወያይ

በዚህ የውይይት ጊዜ ተሳታፊዎች በህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ዙሪያ ጠቃሚ መረጃዎች እንዳገኙ ይገመታል። በተጨማሪም የራሳቸውን ገጠመኝ፣ ያደጉበትን ሁኔታና አሁን በአካባቢያቸው በህፃናት ላይ ስለሚደርሱ አደጋዎች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ጠቃሚ መረጃዎችን ተለዋውጠዋል። ወላጆች ይህንን በተመለከተ ከጎረቤቶቻቸውና ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ ጋር መረጃዎች እንዲለዋወጡ መንገር ያስፈልጋል።

በመቀጠልም የእለቱን የውይይት ፍሬ ሀሳብ ለማስታወስ የሚረዳ በራሪ ወረቀት ለወላጆች መስጠት ያስፈልጋል። ወላጆች ይህንን ወረቀት በጥንቃቄ በመያዝ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጎረቤቶቻቸውና ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ ጋር እንዲያነቡት የቤት ስራ መስጠት ይገባል። በመጨረሻም ተሳታፊዎች በዛሬው ውይይት ላደረጉት ተሳትፎ ማመስገን ያስፈልጋል።

አወያይ

በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከውይይቱ የተገኙ ጠቃሚ ትምህርቶችን ወይንም አዳዲስ ተሞክሮዎችን በተመለከተ አወያይ ማስታወሻ ሊፅፉ ይገባል። ይህም በቀጣይ የአወያዮች ስልጠና ጊዜ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለማስታወስና መፅሀፉ እዱን ለማሻሻል የሚረዱ ሀሳቦችን ለማሰባሰብ ይጠቅማል።

ክፍል ሁለት፡- ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዴት የህፃናት ደህንነትን ማረጋገጥ ይችላሉ?

ለውይይቱ የተመደበው ጊዜ ፡ ስድሳ ደቂቃ

ተግባር 1፡ ያለፈውን የውይይት መርሀ ግብር መከለስ (አምስት ደቂቃ)

> አወያይ
>
> የእለቱ ውይይት ከመጀመሩ በፊት ሁለት ተሳታፊዎች ይምረጡና ባለፈው ውይይት ስለተነሱ ጉዳዮች ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦችን እንዲገልፁ ከታች የተቀመጡትን ትያቄዎች ያቅርቡላቸው

ለውይይቱ ተሳታፊዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

1. ባለፈው የተወያየንባቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
2. በአካባቢያችን በህፃናት ደህንነት ላይ ችግር የሚያስከትሉ ነገሮችን በተመለከተ በተወያየነው መሰረት በቤታችሁና በአካባቢያችሁ ምን ምን ተግባራት አከናወናችሁ?
3. ተሞክሯችሁን ለጎረቤቶቻችሁና ለአካባቢያችሁ ማህበረሰብ አካፈላችሁ?

የውይይቱ አላማ

በውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎች፡-

- ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዴት የህፃናት ደህንነትን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ይገልጻሉ።
- ወላጆች/አሳዳጊዎች እነዴት አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮችን መከላከል እንደሚችሉ ይናገራሉ።

ተግባር ሁለት፡ ለእለቱ የመወያያ ጉዳይ መንደርደሪያ (አስር ደቂቃ)

> አወያይ
>
> ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነጥቦች ለተሳታፊዎች ያንብቡላቸው።

የእለቱ የመወያያ ርእሰ ጉዳያችን ስለህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ነው።

በተጨማሪም ወላጆች ልጆችን እንዴት አደጋ ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች መከላከል እንደሚችሉ ግንዛቤ ያስጨብጣል።

- የእለቱ የመወያያ ርእሰ ጉዳያችን ወላጆች እንዴት የህፃናት ደህንነትን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ይዳስሳል።
- ህፃናትን ከጥቃት ለመከላከል በመጀመሪያ ራሳችን ህፃናትን ከማጥቃት መጠበቅ አለብን።
- ለህፃናት የማይስማሙ ጎጂ ጠባዮች ካሉን ለመለወጥ መማር ያስፈልገናል።
- በህፃናት አያያዝ ችግር ያለባቸውን ወላጆች ባለሙያዎች እንዴት ስሜታቸውን መቆጣጠር እንደሚችሉ በማስተማር ሊረዱአቸው ይችላሉ።
- ጥቃቶች ለምሳሌ፡- አእምሯዊ ጥቃት ወይንም ለልጆች ፍላጎት ምላሽ መንፈግ ደግሞ ጥልቅ ጠባሳ ይተዋል።
- ህፃናትን ከአእምሯዊ ስሜት ጠባሳ ለመከላከል ህፃናትን ለችግር የሚዳርግ ሁኔታን መለየትና መለወጥ ተገቢ ነው። በማንኛውም ሰው ህፃናት ላይ የተለያዩ ጥቃቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ። ለምሳሌ በትላልቅ ህፃናት፣ በዘመዶች፣ በቤተሰብ፣ በጎረቤት፣ በመምህራንና በመሳሰሉት፡ ችግሩ ይፈጸማል።

አወያይ፡

ከውይይቱ በፊት ለመነሻ የሚሆኑ ተሳታፊዎች የሚከተለውን ተጨማሪ መንደርደሪያ ሃሳብ ያቅርቡ።

ህፃናት ውድ የህዝብ ሀብት ናቸው። ነገር ግን ዘወትር ራሳቸውን ከአደጋ የመከላከል ክህሎትና አቅም የላቸውም። ስለዚህ የህፃናትን ደህንነት የመጠበቅ እንዲሁም ራሳቸውን ከአደጋ የመከላከል ክህሎት ማስተማር የወላጆችና የመምህራን ሃላፊነት ነው። እያንዳንዱ ቤተሰብና ትምህርት ቤት ልጆቹን ስለ ደህንነትና መከላከል እርምጃዎች ማስተማር አለበት። እንደ ወላጅ በልጆቻችን ህይወት ዙሪያ ያለውን ነገር በንቃት መከታተልና ልጆቻችንን ማድመጥ ይኖርብናል። ስለዚህም ልጆቻችን በራሳቸው የሚተማመኑ እንዲሆኑና ራሳቸውን ሊያጋጥማቸው ከሚችል አደጋ መከላከል እንዲችሉ ማስተማር ይኖርብናል። በተጨማሪም ቤታችን ስጋት የሌለበትና የልጆቻችን ፍላጎት የሚሚላበትና ድጋፍ የሚያገኙበት መሆን አለበት።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣውና ሀገራችን ተቀብላ ባፀደቀችው የህፃናት መብት ስምምነት እያንዳንዱ ሰው ለህፃናት እንክብካቤና ከለላ የመስጠት ሃላፊነት እንዳለበት ተደንግጓል። ይህ የሀገራችን ህገ መንግስት አካል የሆነው የህፃናት መብት ስምምነት ሁሉም ህፃናት ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የማግኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ህፃናት ከማንኛውም ጉዳት፣ በደል ወይም ጥቃት የመጠበቅ መብት አላቸው። ይህ መብት እንዲከበር ወላጆችና ከህፃናት ጋር የሚሰሩ ሁሉ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል።

ተሳታፊዎች በሶስት ቡድን እንዲከፈሉ ይንገሯቸው።

ለእያንዳንዱ ቡድን የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን የያዙ ሁለት አጫጭር ፅሁፎችን ይስጧቸው።

ቡድኖቹ ታሪኮቹን አንብበውና ተወያይተው ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ እንደሚሰጡ ይንገሯቸው።

እያንዳንዱ ቡድን አወያይ ይምረጥ እንዲሁም የውይይቱን ቃለ ጉባኤ የሚፅፉና በኋላ ለተሳታፊዎች የሚያቀርቡ ተወካዮች መምረጥ ያስፈልጋል።

ታሪኮቹን በተመለከተ ለቡድኖች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ከሰማችሁት ገጠመኝ ውስጥ በህፃናት ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉት ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?

2. በገጠመኙ ውስጥ የተጠቀሱ ህፃናት መጨረሻቸው ምን ሊሆን ይችላል?

ታሪክ አንድ ‑ የደበላ አስተዳደግ

ደበላ አራት አመት ስለሞላው ወደ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊሄድ ነው። ደበላ ሃይለኛና የሚፈልገውን በጉልበቱ ማድረግ የሚፈልግ ልጅ ነው። ደበላ ወንድሙ ጫላ ወይንም ሌሎች ልጆች የሚጫወቱበትን እቃ ሲፈልግ ሄዶ በጉልበት ይቀማቸዋል። ልጆቹ መጫወቻቸውን መስጠት ካልፈለጉ ደበላ ይመታቸዋል። ስለዚህም እናቱ ደበላን መቆጣጠር አልቻለችም። የጎረቤት ልጆች ወላጆች ለደበላ አባት ስሞታ ያቀርባሉ። በዚህ የተነሳ የደበላ አባት በባለቤታቸውና በደበላ ይበሳጫሉ። እንዲያውም ደበላን በየእለቱ በጣም ይገርፉታል። በተጨማሪም የደበላ እናት

ልጇን በአግባቡ በመቅጣት ስርአት ስላላስተማረችው ይጮኹባታል፣ ይደበድቧታል። የደበላ ጠበኝነት ግን በየእለቱ እየባሰበት ነው።

<u>ታሪክ ሁለት፡- የሚሚና የአስጠኚዋ ግንኙነት</u>

ሚሚ አሁን የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ ስትሆን የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ናት። ሚሚ ቆንጆ ልጅ ስትሆን ከሴቶች ይልቅ ከወንዶች ልጆች ጋር መጫወት ትወዳለች። ሚሚ በሃያዎቹ እድሜ ላይ ያለውን መልከ መልካም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህሯን በጣም ትወደዋለች። የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህሯን ጋሼ በማለት ትጠራዋለች። ሚሚ በትምህርቷ ጎበዝ ተማሪ ስለሆነች መምህሯ በክፍል ውስጥ በጣም ያደንቃታል። የቤት ስራ እንድትሰራ ያሰበ መስሎ ዘወትር ወደ ቢሮ ይጠራታል። ሚሚ የስምንት አመት እድሜ ላላት እህቷ ገነት ከመምህር ጋሼ ጋር እንዴት ፍቅር እንደያዛት ትነግራታለች። በተጨማሪም ለገነት በትምህርት ቤታቸው ሰባተኛ ክፍል ከሚገኝ አንድ ተማሪ ጋርም ፍቅር እንደያዛት ትነግራታለች።

ሚሚ ለገነት ራቁታቸውን ሆነው የሚሳሳሙ ወንድና ሴት ስእል ታሳያታለች። ሚሚ ለእህቷ ብዙ ጊዜ ከጋሼ ጋር ቢሮ ውስጥ እንዲሁም ሰባተኛ ክፍል ከሚማረው ልጅ ጋር ባዶ ክፍል ውስጥ ራቁቷን እንደምትሆንም ትነግራታለች።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ሚሚ የከንፈር ቀለምና የጥፍር ቀለም ለመቀባት እናቷን ፈቃድ ትጠይቃለች። ሚሚ ራሷን ስታጊያጊጥ ረዥም ሰአት ስለሚወስድባት ከትምህርት ቤት ማርፈድ ትጀምራለች። ሚሚ ዘወትር የቤተሰብ ስብሰባ ሲኖር ከእድሜ እኩያዎቿ ይልቅ ከትላልቅ ወንዶች ጋር መሆን ትፈልጋለች።

የቡድን ሪፖርት ማቅረብ (አስራ አምስት ደቂቃ)

አወያይ፡

1. ተሳታፊዎች ከላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ከተወያዩ በኋላ በተወካዮቻቸው አማካኝነት በየተራ መልሶቻቸውን ለሌሎች ለተሳታፊዎች መግለፅ ይኖርባቸዋል።
2. ለእያንዳንዱ ቡድን አቅራቢዎች ሶስት ደቂቃ ብቻ በመፍቀድ የቡድናቸውን መልስ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።
3. አንዱ አቅራቢ ሲጨርስ ሁለት ተሳታፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ ወይንም ጥያቄ እንዲያቀርቡ ይፈቀድላቸው።

ከተሳታፊዎች በተሰጡ አስተያየቶች ላይ አወያይ እርማት መስጠት ወይም ሀሳቡን ማጠናከር ይኖርባቸዋል።

አወያይ

ከተሳታፊዎች መካከል የህፃናትን አካላዊ፣ ስሜታዊና ወሲባዊ ጥቃት እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይጠይቁ።

ለፍተሻ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በእለቱ ምን ያህል እንደተማሩ ለመገምገም እንጂ ፈተና ያለመሆኑ ለወላጆች ሊገለፅላቸው ይገባል።

ቁልፍ መልእክቶች (አምስት ደቂቃ)

አወያይ

ቁልፍ መልእክቶችን ለተሳታፊዎች ያንብቡላቸው

- ወላጆች ህፃናት ጤናማ ምርጫ እንዲያካሂዱ ማዘጋጀት አለባቸው።
- በቤት ውስጥ በየእለቱ ልጆች የሚያጋጥማቸውን ነገር የሚናገሩበትና በግልፅ ውይይት የሚያካሂዱበትን መድረክ መፍጠር አስፈላጊ ነው።
- ወላጆች ልጆቻቸው ጥቃት እንደደረሰባቸው ጥርጣሬ ካደረባቸው በብልሃት ለመርዳት መሞከር ተገቢ ነው። ወላጆች በህፃናት ላይ ጥቃት ከሚፈፅሙ ሰዎች ጋር በስርአት መነጋገር ከቻሉ ወይንም በልጆች ላይ ጥቃት ሲፈፀም ለፖሊስ ወይንም በአካባቢያቸው የህፃናትን ጥቃት የመከላከል ሀላፊነት ላለው አካል ጥቆማ ከሰጡ ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን ልጆች ከጥቃት መከላከል ይችላሉ።
- በቤትም ሆነ ከቤት ውጪ ትላልቅ ሰዎች ወይንም በእድሜ ከፍ ያሉ ሰዎች ከልጆቻችሁ ጋር በጣም ተቀራርበው ከተመለከታችሁ መጀመሪያ ምንም አይነት ፍንጭ ሳትሰጡ በጥንቃቄ ክትትል አድርጉ። ልጆቻችሁ ከማን ጋር ምን በማድረግ ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉ እወቁ። ይህ ክትትል በልጆች ላይ ሊመጣ ከሚችል አደጋ እንድንጠነቀቅ ይረዳል።
- የእለት ውሏችሁን የመናገር ልምድ አዳብሩ። ልጆቻችሁም ተመሳሳይ ልምድ እንዲያዳብሩ

አወያይ

በዚህ የውይይት ጊዜ ተሳታፊዎች በህፃናት ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ጠቃሚ መረጃዎች እንዳገኙ ይገለፅላቸው።

በተጨማሪም የራሳቸውን ገጠመኝ፣ ያደጉበትን ሁኔታና አሁን በአካባቢያቸው በህፃናት ላይ ስለሚደርሱ አደጋዎች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ጠቃሚ መረጃዎችን ተለዋውጠዋል። ወላጆች ይህንን በተመለከተ ከጎረቤቶቻቸውና ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ ጋር መረጃዎች እንዲለዋወጡ መንገር ያስፈልጋል።

በመቀጠልም የእለቱን የውይይት ፍሬ ሀሳብ ለማስታወስ የሚረዳ በራሪ ወረቀት ለወላጆች መስጠት ያስፈልጋል። ወላጆች ይህንን ወረቀት በጥንቃቄ በመያዝ ከቤተሰቦቻቸውና ከጎረቤቶቻቸውና ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ ጋር እንዲያነቡት የቤት ስራ መስጠት ይገባል። በመጨረሻም ተሳታፊዎች በዛሬው ውይይት ላደረጉት ተሳትፎ ማመስገን ያስፈልጋል።

አመቻቹ ማስታወሻ ይያዙ

በውይይቱ መጨረሻ ከውይይቱ የተገኙ ጠቃሚ ትምህርቶች ወይንም አዳዲስ ተሞክሮዎች በተመለከተ ማስታወሻ መፃፍ ይገባል። ይህም በቀጣይ የግንኙነት ጊዜ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለማስታወስና መጽሀፉ እዱን ለማሻሻል የሚረዱ ሀሳቦችን ለማሰባሰብ ይጠቅማል።

ለአወያይ ተጨማሪ መረጃ

## ወላጆች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

አወያይ

ህፃናት ስለሚኖሩበት አለም ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አላቸው። ስለዚህም ዘወትር እድገታቸውንና ደህንነታቸውን ከሚፈትኑ ምርጫዎች ጋር ይጋፈጣሉ። ወላጆች ልጆቻችንን ከአደጋ ለመከላከል የልጃችንን ደህንነት በተመለከተ መርህ ግብር በመያዝ መተግበር ይገባናል። መርህ ግብራችን የሚከተሉትን አምስት ተግባራት ሊይዝ ይገባል።

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አምስት ነጥቦች ለተሳታፊዎች ያንብቡላቸው። ወላጆች ይህንን መተግበር ከቻሉ የልጆቻቸው ደህንነት በጤናማ ሁኔታ ላይ መሆኑን ወይንም አለመሆኑን ለመገንዘብ ያስችላቸዋል።

1. ዝግጅት፡ ወላጆች ልጆቻችን ተገቢና ጤናማ ምርጫ መወሰን እንዲችሉ ጥሩ ትምህርትና አመራር የመስጠት ግዴታ አለባቸው። ስለዚህም ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር መነጋገር መቻላቸው ትልቅ

ጅምር ነው። ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር የመወያየት ባህል ሲፈጥሩ ህፃናት ራሳቸውን ለመርዳት እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን ለመርዳት የሚያስችላቸውን ጥሩ መንገድ ይፈጥራሉ።

2. መጠየቅ፡ ልጆች ከወላጆች ተለይተው በነበሩበት ጊዜ ከማን ጋር ምን ሲያደርጉ/ሲነጋገሩ እንደነበረ በፍቅርና በተረጋጋ ሁኔታ የመጠየቅ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። ብዙ ጊዜ ህፃናትን ሰው አይጎዳቸውም። የሚለው አመለካከት አዘናጊ ሊሆን ይችላል። ልጆች ከቤታቸው ውጪ በነበሩበት ጊዜ ስለነበሩበት ሁኔታ መጠየቅ የተከሰቱ ችግሮችን ወዲያው አውቀን እርምት ለማድረግና ወደፊት ሊያጋጥሙን የሚችሉ ችግሮችንም ለመከላከል ይጠቅማል።
3. ማድመጥ፡ ወላጆች ልጆች በራሳቸው ተነሳሽነት በየእለቱ የሚነግሯቸውን ነገር በትኩረት ማድመጥ አለብን። ወላጆች አንዳንድ ጊዜ ልጆች ፈጥረው የሚያወሩ የሚመስሉ ነገሮች የእውነት ሊሆን ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።
4. ማወቅ፡ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ጠባይ ማወቅ አለባቸው። ከልጆቻቸው ጋር የሚውሉ ልጆችና አዋቂዎችን ጠባይ በውል ማወቅ ይገባቸዋል።
5. ማስተማር፡ ወላጆች ልጆቻቸውን እንደግንዛቤያቸው ደረጃ ማስተማር ይገባቸዋል። ልጆችን ከጥቃት የመከላከል ትምህርቱ የሚጀምረው ስለ ሰውነታቸው ክፍሎች በማሳወቅ ነው። ህፃናት የሚነገራቸውን መረዳት ከሚጀምሩበት እድሜ በኋላ ሌሎች ሊነኳቸውና ስለማይገቡ የሰውነት ክፍሎች በግልጽ ሊነገራቸው ይገባል። ልጆች ማድረግ ስላለባቸውና ማድረግ ስለሌለባቸው ነገሮች ሊማሩ ይገባል። ልጆች ያዩትን፣ የሰሙትን፣ ያደረጉትን፣ የተናገሩትን፣ ሌሎች ያደረጉትንና የተናገሩትን ለወላጅ መናገር አስፈላጊ መሆኑን ማስተማር ተገቢ ነው። ይህም ህፃናት ስለውሏቸው የተፈጠሩ ክስተቶችን፣ ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን እንዲያጋሩን ያስችላል።

## *ህፃናት ጉዳት እንደ ደረሰባቸው የሚያመላክቱ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማወቅ*

ጉዳት የደረሰባቸው ህፃናት የሚያሳዩት የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ማወቅ በፍጥነት አስፈላጊውን እርምት ለመስጠትና ህፃናትን ከችግሩ ለማውጣት የተሻለ አጋጣሚን ይፈጥራል።

አወያይ

የህፃናት ጥቃቶች ብዙ ጊዜ ግልፅ አይደሉም። የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን መማር በተቻለ ፍጥነት ችግሩን ለመለየት እንዲሁም ጥቃት ለተፈፀመባቸው ህፃናትና ለጥቃት ፈፃሚዎች የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ ለማድረግ ያስችላል። ስለ ህፃናት ጥቃት ከልጆች ጋር መነጋገር አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በጣም ጠቃሚ ነው። ዘዴዎችን ከባለሙያ ሊያስፈልግ ይችላል።

ልጆችን ከጥቃት ለመከላከል ወላጆች መውሰድ ያለባቸው የመጀመሪያው እርምጃ በቤት ውስጥ ግልፅ ውይይት ማድረግ ነው። ህፃናት ዘወትር ስለ ደረሰባቸው ጥቃት ላይናገሩ ይችላሉ። ስለዚህም ወላጆች ሌሎች ምልክቶችን በንቃት መመልከት አለባቸው። የህፃናት ጥቃትን ለመለየት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች ከተሳታፊዎች ጋር ተወያዩባቸው።

ፍንጭ፦ ተዘዋዋሪ መልእክት፡ ህፃናት ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ወደ ጓደኛ ወይንም ዘመድ ቤት ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆን ሊያሳዩ ይችላሉ። ባልተለመደ ሁኔታ የተወሰነ ሰውን ለመቅረብ አለመፈለግ (ቀድሞ የሚቀርቡትን ሰው መሸሽ) ወይም በተቃራኒው ቀድሞ ቅርበት ካልነበረ ሰው ጋር ድንገት ልዩ ቀረቤታ መፍጠር ሌላው ፍንጭ ነው።

ጫፍ የወጡ ጠባዮችን ማሳየት፡ በጣም መማረር ወይንም አንድን ነገር በጣም መፈለግ፣ በጣም ዝም ማለት ወይንም በጣም ቁጡ መሆን ህፃናት ጉዳት እንደደረሰባቸው ሊያሳየን ይችላል።

- ከወላጆች ወይንም ከሞግዚቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው አለመምሰል
- ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን ማሳየት፤ ለምሳሌ እንደትልቅ ሰው ሌሎች ህፃናትን መንከባከብ ወይንም እንደ ህፃን ልጅ መወዝወዝ፣ ጣት መጥባት፣ በቁጣ መገንፈል በምልክትነት ሊታዩ ይችላሉ።

አካላዊ ጥቃትን ጠቋሚ ምልክቶች

- ተደጋጋሚ ቁስል ወይንም ሰንበሮች ወይንም ጠባሳ
- ተመሳሳይ ቅርፅ ያለው ቁስል በእጅና በሆድ አካባቢ መታየት
- ሰዎች እንዳይነኳቸው መሸሽ፣ በድንገተኛ እንቅስቃሴዎች መደንበር ወይንም ወደ ቤት ከመሄድ መፍራት
- ቁስልን ለመሸፈን ልጅን ተገቢ ያልሆነ ልብስ ማልበስ ለምሳሌ፦ በሞቃት ቀናት ረዥም ኮሌታ ያላቸው ሸሚዞች መልበስ

በህፃናት ላይ ወሲባዊ ጥቃት መድረሱን የሚጠቁሙ ምልክቶች

- ባልተለመደ ሁኔታ ለመራመድም ሆነ ለመቀመጥ መቸገር
- ለእድሜያቸው ተገቢ ያልሆነ ወሲባዊ እውቀት ወይንም ፍላጎት ማሳየት
- ሁልጊዜ ንቁ መሆን እንዲሁም መጥፎ ነገር እንደሚከሰት በመጠበቅ ንቁ መሆን
- የመዳራት ጠባይ ማሳየት
- ባልታወቀ ምክንያት የተወሰነ ሰው ፈፅሞ መጥላት
- በሌሎች ሰዎች ፊት ልብስ ለመቀየር ፈቃደኛ ያለመሆን ወይንም በአካላዊ እንቅስቃሴዎች አለመሳተፍ

- በብልት አካባቢ እንደ መቧጨርና መቅላት የመሳሰሉት ምልክቶች መታየት
- ባልተጠበቀ ሁኔታ አልጋ ላይ መሽናት፣የምግብና የእንቅልፍ ፍላጎት ማጣት
- ጥቃቱን ያደረሰባቸውን ሰው ሲመለከቱ መፍራትና መደንገጥ
- ከሌሎች ሰዎች መገለል
- ራስን የመጥላትና ስለራስ ጥሩ ስሜት አለመኖርና (ራስን መጣል)
- ከቤት መጥፋትና የመሳሰሉት ምልክቶች ወሲባዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው ያመለክታል።

ለህፃናት ፍላጎት ምላሽ የመንፈግ ጥቃት መድረሱን የሚጠቁሙ ምልክቶች

- ልብስን በአግባቡ አለመልበስ፣ የልብስ በጣም መቆሸሽ ወይንም ለወቅት ተስማሚ ያለመሆን
- በተደጋጋሚ የንፅህና ችግር መታየት ለምሳሌ መቆሸሽ፣ የፀጉር መቆጣጠርና አለመታጠብ፣የእጅ እና የእግር ጥፍር ማደግ፣ በግልፅ የሚታወቅ የሰውነት ጠረን
- ህክምና ያላገኘ በሽታና አካላዊ ቁስል
- በተደጋጋሚ ተመልካች ማጣት፣ ልጆች ጥሩ ባልሆኑ ቦታዎች ወይንም ሁኔታዎች እንዲጫወቱ ብቻቸውን መተው
- በተደጋጋሚ ከትምህርት ቤት ማርፈድ ወይንም መቅረት
- የትምህርት ውጤታቸው ዝቅ እያለ መምጣት በምልክትነት ሊወሰድ ይችላል።

አወያይ

ወላጆች ከላይ የተዘረዘሩትን ምልክቶች በተደጋጋሚ ከተመለከቱ ልጆቻቸው የእነርሱን ድጋፍ ማግኘት እንደሚፈልጉ ያስረዱዋቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅርና በትእግስት ስለውሏቸው ማነጋገር ይገባቸዋል። ወላጆች የልጆቻቸውን ችግር መለየት ከቻሉ እንዴት መለወጥ እንዳለባቸው ማሰብ አለባቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን መርዳት ካልቻሉ በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ጤና ተቋማት በመውሰድ የህክምና ባለሙያ ማማከር ይገባቸዋል።

ህፃናትን ከጥቃት ለመከላከል ምን ማድረግ ያስፈልጋል**?**

አወያይ

ህፃናት ላይ ጥቃት እንዳይደርስ የተሌዩ እርምጃዎች ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ይጠበቃሉ። ተሳታፊዎች እነኚህን እርምጃዎች መገንዘብ እንዲችሉ ከዚህ በታች ተዘረዘሩትን እርስዎ አስቀድመው በማጥናት ያወያዩዋቸው

- ለልጆች ጊዜ መስጠት አለብን።
- ሁልጊዜም ከጥቃት የተጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብን።
- ወላጆች በልጆቻቸው ላይ በተደጋጋሚ የሚታዩ ጤናማ ያልሆኑ ምልክቶችን ወይም ጥቃት መድረሱን የሚጠቁሙ ምልክቶች በማየት ተገቢውን እርዳታ መስጠት ያስፈልጋል።

ህፃናትን ከወሲባዊ ጥቃት መከላከል

ወሲባዊ ጥቃት ከአካላዊ ጉዳት በተጨማሪ የሚያስከትለው ስሜታዊ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው።

- ወሲባዊ ጥቃት በህፃናት ላይ የሀፍረትና የወንጀለኝነት ስሜት ይፈጥራል።
- ህፃናት በደረሰባቸው ጥቃት ራሳቸውን ይኮንናሉ።
- የወሲባዊ ጥቃት ሀፍረት ህፃናት የደረሰባቸውን ለወላጆቻቸው እንዳይናገሩ ያደርጋቸዋል።
- ወላጆቻቸው ወይንም ሞግዚቶቻቸው እንደማያምኗቸው፣ እንደሚናደዱባቸው ወይንም ቤተሰብ በእነርሱ ምክንያት እንደሚለያይ በማሰብ ይጨነቃሉ።
- ራሳቸውን ለመጥላት እንዲያውም ለመሞት እስከ መወሰን ያደርሳል።
- ለከባድ የአእምሮ ህመም ሊያጋልጣቸው ይችላል።

አወያይ

ሕፃናት የደረሰባቸው ጥቃት በራሳቸው ላይ ያመጡት ራሳቸው እንደሆኑ ወይንም ባልታወቀ ምክንያት እንደመጣባቸው ይሰማቸዋል።

ይህንን አመለካከት ለመቀየር ወላጆች በቤተሰብ ውስጥ ግልፅነት፣ የፍቅር ግንኙነት እንዲሁም በእራት ሰአት ስለ ቀን ውሏቸው የማውራት ልምድ ሊያዳብሩ ይገባል። ወላጆች ለማመን የሚቸገሩበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ጉዳዩን በትኩረት ማጥናት ይገባቸዋል።

ወላጆች ከልጆች የሰሙትን ነገር ሳይመረምሩ ችላ ማለት ወይንም እንደውሸት መውሰድ አይገባቸውም።

ለህፃናት ችግር ትኩረት መስጠት

- ብዙ ጊዜ ለወላጆች ህፃናትን ችላ ማለት ምን እንደሆነ ማሳየት ቀላል አይደለም። ነገር ግን ልጆች ችላ የሚባሉበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ፡-

- አንዳንድ ጊዜ ወላጆች ከፍተኛ ጉዳት ያጋጥማቸውና ወይንም የስሜት መረበሽ ይደርስባቸውና ልጆቻቸውን መንከባከብ ያቅታቸዋል።
- አንዳንድ ወላጆች ደግሞ በአልኮሆል ወይንም በጫት ወይንም በሌሎች አደንዛዥ እፆች ሱስ በመያዛቸው ልጆቻቸው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ አያስተውሉም።
- ከመጠን በላይ ስራ የሚበዛባቸው ወላጆች ለልጆቻቸው ችግር ትኩረት ላይሰጡ ይችላሉ።

ወላጆች በልጆች ላይ ጥቃት እንደተፈፀመ ጥርጣሬ ሲያድርባቸው ማድረግ ያለባቸው ምንድን ነው**?**

ወላጆች በልጆች ላይ ጥቃት እንደተፈፀመ ጥርጣሬ ካደረባቸው በቅድሚያ፡

- ህፃናቱን መንከባከብና ማረጋጋት አለባቸው።
- ከልጆች ጎን መቆም ይገባቸዋል።
- የልጆቹን ደህንነት ለመጠበቅ ጉዳዩን ለሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
- ከህክምና ባለሙያዎች እርዳታ መጠየቅ ይገባል።

አወያይ

ጥቃት የደረሰባቸውን ልጆች ጉዳይ ለሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት ማሳወቅ ወደ ፊት የከፋ ጥቃት እንዳይከሰት ለማድረግ ያስችላል። ወሲባዊ ጥቃት የተፈፀመባትን/የተፈፀመበትን ህፃን በአስቸኳይ ወደ ጤና ተቋም በመውሰድ አስፈላጊውን ምርመራ በማድረግ ህፃናቱን ሊደርስባቸዉ ከሚችለዉ የተለያዩ የአባለዘር በሽታዎች መታደግ ይቻላል።

በልጆች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል እንዲቻል ለወላጆች ተጨማሪ ጥቆማዎች

- ወላጆች በቤተሰብ ውስጥ የእለት ውሏቸውን በመናገር ለልጆች የግልፅነት ምሳሌ መሆን አለባቸው። ልጆችም የእለት ውሏቸውን እንዲናገሩ ማበረታታት ይገባል።
- ልጆች በመጥፎ አጋጣሚዎች መሳተፋቸውን ሲናገሩ ልትወቅሷቸው ወይንም ልትጮሁባቸው አይገባም። ልጆች በመጥፎ ሁኔታዎች በመሳተፋቸው ከተናደዳችሁ ወይንም የምትጮሁባቸው ከሆነ ወደፊት እንዲህ አይነት አጋጣሚዎችን አይነግሯችሁም።

- ልጆች በመጥፎ አጋጣሚዎች መሳተፋቸውን ሲናገሩ ልክ ጥሩ ስራ ሲሰሩ እንደምታደርጉት ልታበረታቷቸው ይገባል። ይሁን እንጂ ስለተደረገው መጥፎ ነገር በርጋታና በጓደኝነት መንፈስ በዝርዝር ምን እንደተደረገ፣ መቼና የት እንደተደረገ እንዲሁም ከማን ጋር እንደተፈፀመ መመርመር ይገባል። ከዚያም ልጆችን ሳያስደነግጡ ስለድርጊቱ መጥፎነት በእርጋታ መግለፅ ይገባል። ከልጆች የተገኘው መረጃ በቀጣይ ምን መደረግ እንዳለበት ለመወሰን ይረዳል።

- በቤታችሁ ዙሪያ ጥልቅ የጎርፍ መውረጃ ወይንም የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ወይንም ያልተደፈኑ ጉድጓዶች ካሉ መደፈናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

- ተቀጣጣይ ምድጃዎችን፣ በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ የአልኮሆል መጠጦችን፣ ኩብሪቶችን፣ ስለታም ነገሮችን፣ መድሃኒቶችን እንዲሁም የግል ንፅህና መጠበቂያ ምርቶችን ህፃናት ከማይደርሱበት ስፍራ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

- ህፃናት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትና የሚጫወቱበት ስፍራ መምረጥ ተገቢ ነው።

- ህፃናት የመኪና መንገድ እንዴት እንደሚያቋርጡ መከታተልና መምራት ይገባል።

- አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሪክ ሶኬቶችን መሸፈን ተገቢ ነው።

- ወላጆች የጎረቤት ልጆችን፣ የዘመድና የጓደኛ ልጆችን ጠባይ ማወቅ ይገባቸዋል።

- ለህፃናት እንደኦቾሎኒ ሞላላ ወይንም ሌሎች ክብ ቅርፅ ያላቸውን ምግቦችና ደረቅ ከረሜላዎችን መስጠት አይገባም።

- ልጆችን በውሃ አካባቢ ወይንም በውሃ ውስጥ ትቶ መሄድ ስለማይገባ አብሮ መቆየት አስፈላጊ ነው።

- ልጆችን ተሸክሞ ትኩስ ነገር መያዝ ፈፅሞ አይገባም።

- ለቀላል ቁስሎች ፈጣን ህክምና ለመስጠት የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን በቤት ውስጥ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

- የቆሰሉ ወይንም ደማቸው የሚፈስ ህፃናትን ለመርዳት ጓንት ወይንም የላስቲክ ከረጢት መጠቀም ከልጆች ወደ ወላጆች ወይንም ከወላጆች ወደ ልጆች በቀላሉ የሚተላለፉ ጀርሞችን ለመከላከል ይረዳል።

ባልታወቁ ሰዎች የሚፈፀም ጠለፋና ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል

- ልጆችን በማያውቁት ስፍራ ብቻቸውን አለመተው

- ልጆችን በገበያ፣ በሃይማኖት ቦታዎችና በሌሎች ቦታዎች ብቻቸውን አለመተው

- ልጆችዎ ዘወትር የት እንደሚሆኑ ማወቅ

- ልጆችን ከሁለት አመት ከስድስት ወር ጀምሮ ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር መነጋገር ጥሩ አለመሆኑን መንገር ያስፈልጋል። ልጆችዎ የማያውቋቸው ሰዎች ሊወስዷቸው ሲሞክሩ ወዲያውኑ እንቢ እንዲሉ ወይንም እንዲጮሁ ያሰልጥኗቸው።

ልጆችን ከእሳትና ከቃጠሎ ለመከላከል

- ክብሪቶችና ሌሎች እሳት ማቀጣጠያዎች ልጆች ከማይደርሱበት ቦታ አስቀምጡ።
- ምድጃዎች ልጆች ከማይደርሱበት ቦታ መቀመጣቸውን አረጋግጡ።
- ትናንሽ ልጆች ምግብ በሚዘጋጅበት ቦታ አለመድረሳቸውን አረጋግጡ።
- ልጆችን በሞቀ ውሃ ለማጠብ ሲፈልጉ አስቀድመው የውሃውን የሙቀት መጠን ከእጅዎት ጀርባ ላይ በማድረግ ይፈትሹ።
- አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሪክ ሶኬቶችን ወንበር፣ ጠረጴዛና የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም ግድግዳዎችን መሸፈን ይገባል።
- ልጆች በሚጫወቱበት አካባቢ የሞቀ ውሃ እንዳይቀመጥ ማድረግ ተገቢ ነው።

ልጆችን ከመርዝ አደጋ ለመከላከል

- በቤት ውስጥ የሚገኙ መርዛማ ነገሮችን ለይታችሁ አስቀምጡ።
- በቤት ውስጥ የሚገኙ መርዛማ ነገሮች ልጆች ከማይደርሱበት ቦታ መቀመጣቸውን አረጋግጡ።
- ሁሉንም መድሃኒቶችና የመድሃኒት መገልገያዎች ልጆች በማይደርሱበት ቦታ አስቀምጡ።
- ልጆችን ከምግብ በስተቀር ሌሎች ነገሮችን ወደ አፋቸው እንዳያስገቡ ማስተማር በመርዛማ ነገሮች የሚመጣውን አደጋ ለመከላከል ጠቃሚ ነው።

ልጆችን በውሃ ከመስመጥ አደጋ ለመከላከል

- ልጆችን ፈፅሞ ብቻቸውን በመፀዳጃ ቤት አለመተው።
- ለመፀዳጃ ቤት መዝጊያ በርና መቆለፊያ በማዘጋጀት በውስጥ በኩል ሰው ከሌለ በስተቀር በውጪ መቆለፍ።
- በወንዝ ወይንም በምንጭ አካባቢ ወይንም በጉድጓድ ውሃ አቅራቢያ ከልጆች ጋር አብሮ መቆየት ይገባል።

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የውሃ ጉድጓዶች አጥር እንዲሰራላቸውና ዘወትር እንዲጠበቁ ከአካባቢያችሁ የአስተዳደር አካላት ጋር መወያየት አስፈላጊ ነው።

ልጆችን ከመኪና አደጋ ለመከላከል

- የመኪና መንገድ ስታቋርጡ የትናንሽ ልጆችን እጅ ያዙ።
- ልጆች ራሳቸውን ችለው የመኪና መንገድ ማቋረጥ መቻላቸውን ለማወቅ የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ ተመልከቱ። እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑ ህፃናትን ፈፅሞ ብቻቸውን መንገድ እንዲያቋርጡ አትፍቀዱላቸው።
- ልጆች በተቻለ መጠን የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ በቀጥታ መንገድ መጠቀም እንዲችሉ በትኩረት ማስተማር ተገቢ ነው።
- ወላጆች የትራፊክ ህግን በመክበር ለልጆች አርአያ መሆን/የመንገድን ግራ ይዞ መጓዝ፣ ተገቢውን የመንገድ መቋረጫ መስመርን/ዜብራ/ ተከትሎ የመኪና መንገድን መሻገር እንዲለምዱ ማድረግ ይገባል።
- ልጆች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትና የሚዝናኑበት ደህንነቱ የተጠበቀ ስፍራ መምረጥ አስፈላጊ ነው።
- ልጆች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ ግራና ቀኝ አይተው እንዲሁም መንገዱ ከተሽከርካሪ ነፃ መሆኑን አይተው እንዲያቋርጡ ማስተማር ይገባል።
- ልጆች በመኪና መንገድ ላይ እንዳይጫወቱ መምከር ያስፈልጋል።
- ልጆችን በመኪና በምናጓጉዝበት ወቅት የፊት ወንበር ወይም የጋቢና ወንበርን አለመጠቀም ተገቢ ነው።

የጨቅላ ህፃናት ደህንነትና ጥበቃ

ሁሉም የመከላከል ተግባራት ለህፃናት አስፈላጊ ቢሆኑም የህፃናት ጤናና እንክብካቤ ዐቢይ የትኩረት መስክ ነው።

- ህፃናትን በቤት ውስጥ ከአደጋ ለመከላከል
    - ✓ በቤታችን በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ አደጋ የማድረስ አቅም ያላቸው ነገሮች አሉ።
    - ✓ ልጆችን ተሸክሞ ትኩስ ነገሮችን መያዝ በፍፁም አይገባም።

- ✓ በህፃናት  አናት ላይ እንዳይወድቅ በህፃናት መኝታ አጠገብ ብርጭቆ፣ አትክልት ወይንም ጌጣ ጌጦችን ከማስቀመጥ መቆጠብ ያስፈልጋል።
- ✓ ወንበርና ጠረጴዛዎች ተረጋግተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ ይገባል።
- ✓ ልጆችን በሞቀ ውሃ ለማጠብ ሲፈልጉ አስቀድመው የውሃውን የሙቀት መጠን ከእጅዎት ጀርባ ላይ በማድረግ ይፈትሹ።
- ✓ ህፃናት ከእይታችሁ ውጪ በሆነ ስፍራ በፍፁም ብቻቸውን አትተዎቸው።

- ህፃናትን ከመታነቅና ከመታፈን ለመከላከል
  - ✓ ጨቅላ ህፃናት ሲተኙ በጀርባቸው ብቻ ማስተኛት፣ ትራስ አለመጠቀም።
  - ✓ ጨቅላ ህፃናት በተኙበት እንዳይታፈኑ በቀላሉ ተተብትበው ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ቁርጥራጭ ጨርቆችና ስፖንጅ መሳይ ነገሮችን ከመኝታቸው ማራቅ። በልጆች አጠገብ ካልሆናችሁ በስተቀር ትራስ፣ ብርድ ልብስ ወይንም አሻንጉሊቶችን በተኙ ህፃናት ፊት ዙሪያ አለማድረግ
  - ✓ በቤታችሁ ከእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ሳንቲሞችን፣ ምስማሮችን፣ ጠጠሮችን፣ ስንጥሮችን፣ ቁልፎችንና ሌሎች ትናንሽ ነገሮችን አግኝተው ወደ አፋቸው እንዳያስገቡ ክፍሎችን ማፅዳት
  - ✓ ህፃናትን መጥነን ማጉረሳችንን ማረጋገጥ
  - ✓ መድሃኒቶችን፣ ቅባቶችንና ኬሚካሎችን ልጆች በማይደርሱበት ቦታ መቀመጡን ማረጋገጥ

## ልጆች ላይ በድንገተኛ አደጋ ለሚደርስ ጉዳት ወላጆች ማድረግ ያለባቸው ዝግጅትና እርምጃ

- ወላጆች ወይንም ሞግዚቶች ለትንንሽ ቁስሎች ፈጣንና ቀላል ህክምና ለመስጠት የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን በቤታችሁ ማዘጋጀት ይገባችኋል።
- ጉዳት የደረሰባቸው ህፃናት የባለሙያ ድጋፍ እስኪያገኙ ድረስ ወላጆች ይህንን የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን በመጠቀም እርዳታ ሊያደርጉላቸው ይችላሉ።
- የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥንን ከካርቶን ወይንም ከላስቲክ ማዘጋጀት ይቻላል። በመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን ውስጥ ጥጥ፣ ቁስል ማሸጊያ ፕላስተር፣ ከመድሃኒት መሸጫ መደብሮች የሚገዙ ቁስልንና ጭረትን ለመጥረግ የሚያገለግሉ ጂቪና እንዲሁም ቁስል መሸፈኛ ንፁህ ቁራጭ ጨርቆች ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

- የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥንን ልጆች በማይደርሱበት ስፍራ ማስቀመጥ ይገባል። በመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን ውስጥ የሚገኙ ነገሮች የተጎዱ ህፃናት ወደ ጤና ተቋማት እስኪደርሱ ድረስ የሚከሰተውን የደም መፍሰስ ለመከላከል ያግዛሉ።

- የተጎዱ ህፃናትን ለመርዳት የሚፈሳቸውን ደም ለማስቆም በሚደረገው ጥረት ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

- ወላጆች የሚደማውን የሰውነት ክፍል ሲነኩ እጆቻቸውን በንፁህ ላስቲክ መሸፈን ያስፈልጋል። ይህም ከልጆች ወደ ወላጆች ወይንም ከወላጆች ወደ ልጆች በቀላሉ የሚተላለፉ ጀርሞችን ለመከላከል ይረዳል።

- ወላጆች የሚደማ ቁስልን፣ ያልተሸፈነ ቁስልን፣ የቆዳ ቁስልን፣ የተቀደደ ቆዳ ወይንም በደም የራሱ ጨርቆችን ሲነኩ እጆቻቸውን በንፁህ ላስቲክ መሸፈን ያስፈልጋቸዋል።

- ልጆች የሌሎች ሰዎችን ደምና የሰውነት ፈሳሽ በፍፁም እንዳይነኩ ማስተማር አለባቸው።